በዚህ መሰረት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በ19 ቀናት ውስጥ የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ይሰጣል::

### *የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት*

- ✓ የማመልከቻ ማጣሪያ ክፍያ ብር 125.00 /መቶ ሃያ አምስት ብር/፣
- ✓ ለኤፍ.ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/፣
- ✓ ለአጭር ወይም ለመካከለኛ ሞገድ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/፣
- ✓ ለቴሌቪዥን ከሆነ ደግሞ ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሺህ ብር/ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ይከፈላል::

### *የሰብስክሪብሽን ብሮድካስት አገልግሎት ሲባል ምን ማለት ነው?*

***የውጪ ብሮድካስት ፕሮግራሞችን /ሰብስክሪብሽን/ በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ አገልግሎት ማለት፡-*** በውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎቶች የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን ለማድረስ በባለፈቃዱ እና በተጠቃሚ መካከል በሚደረግ ስምምነት ለዚሁ አገልግሎት ሲባል የተዘጋጀውን ልዩ መሳሪያ ወይም የሚስጥር ቃል በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ነው::

### *የሰብስክሪብሽን /የውጭ ብሮድካስት ፕሮግራሞች/ ፈቃድ ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?*

- ✓ በአግባቡ የተሞላ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ፣
- ✓ የፕሮጀክት ጥናት፣
- ✓ ከዋናው ድርጅት /ከቻሉ ባለቤት/ጋር የተዋዋሉበትን ሰነድ፣
- ✓ የአመልካች ድርጅት የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣



ማንኛውም ድርጅት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ አዲስ ፈቃድ በ4 ቀን ከ1 ሰአት፣ እንዲሁም ተጨማሪ የቻናል እውቅና ከሆነ ደግሞ በ3 ቀን ውስጥ አገልግሎት ማግኘት ይችላል::

### *የሰብስክሪብሽን /የውጭ ብሮድካስትፕሮግራሞች/ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት ምን ያህል ክፍያ ይጠይቃል?*

- ✓ የማመልከቻ ቅፅ ክፍያ ብር 50.00 /ሃምሳ ብር/፣
- ✓ የማመልከቻ ማጣሪያ ክፍያ ደግሞ ብር 400.00 (አራት መቶ ብር)፣
- ✓ ለሬዲዮ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/፣
- ✓ ለቴሌቪዥን ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/፣
- ✓ ለሬዲዮ እና ለቴሌቪዥን ከሆነ ደግሞ ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ ብር/፣
- ✓ ለተጨማሪ ቻናል እውቅና ደግሞ ብር 3,000.00 (ሦስት ሺህ ብር) ለባለስልጣን መ/ቤቱ በመክፈል አገልግሎት ማግኘት ይቻላል::

በመጨረሻም ማንኛውም ሰው ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ የብሮድካስት አገልግሎት እንዳይሰጥ ወይም እንዳያሰራጭ የኢትዮጵያ ብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ አንቀፅ 18 ቁጥር (1) (2) የተደነገገውን ያስገነዝባል:: ስለዚህ እያንዳንዱ ዜጋ የብሮድካስቱን አዋጅ አክብሮና ጠብቆ መስራት ይጠበቅበታል:: እንዲሁም ይህን አክብረው በማይሰሩ አካላት ለባለስልጣኑ የማሳወቅ አገራዊ ግዴታው በንቃት ሊሳተፍ ይገባል ::



## *የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*
## *The Federal Democratic Republic of Ethiopia*

## *የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን*
## *Ethiopian Broadcasting Authority*

# *የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች*


| | |
|---|---|
| ስልክ/Tel: | 251-0115538760/59 |
| ፋክስ/Fax: | 251-0115536750 |
| ኢ. ሜይል/E Mail: | e.b.al@ethionet.et |
| ድረ-ገጽ/Website: | WWW.eba.gov.et |
| የመ.ሣ.ቁ/P.O.BOX: | 43142 |

## *የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች*

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 533/99 ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አንዱ ለብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ መስጠት ነው:: ፈቃድ የሚሰጣቸው የብሮድካስት አገልግሎቶችም ***በሶስት*** ይከፈላሉ:: እነሱም:-

1. የመንግስት /የህዝብ/ ብሮድካስት አገልግሎት
2. የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት
3. የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ናቸው::

የእነዚህ የብሮድካስት አገልግሎቶች ምንነትና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል::

***የመንግስት /የህዝብ/ ብሮድካስት አገልግሎት ማለት:-*** ህዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅና ለማዝናናት በአገር አቀፍ ወይም በክልል የሚቋቋም ተጠሪነቱም ለፌደራል የህዝብ ተወካዮች ወይም ለክልል ምክር ቤቶች የሆነ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግስት በጀት የተመደበለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው::

### *የመንግስት /የህዝብ/ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?*

- ✓ በአግባቡ የተሞላ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
- ✓ የፕሮጀክት ጥናት፣
- ✓ የድርጅቱ አመራር አባሎች የስራ ልምድና የትምህርት ማስረጃ ሰነድ፣
- ✓ የድርጅቱ ተጠሪና የባለአክሲዮኖች መታወቂያ ኮፒ /ቅጂ/፣



### *የመንግስት /የህዝብ/ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት ምን ያህል ክፍያ ይጠይቃል?*

በዚህ መሰረት የመንግስት ብሮድካስት አገልግሎት ለማግኘት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በ17 ቀናት ውስጥ ፈቃድ ማግኘት ይችላል::

### *የመንግስት ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት*

- ✓ ለማመልከቻ ማጣሪያ ክፍያ ብር 250.00 /ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/፣
- ✓ የተሰጠው ፈቃድ ለኤፍ.ኤም ከሆነ ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሺህ ብር/፣
- ✓ ለአጭር ወይም ለመካከለኛ ሞገድ ከሆነ ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/፣
- ✓ ለቴሌቪዥን ከሆነ ደግሞ ብር 60,000.00/ ስልሳ ሺህ ብር/ የመጀመሪያ የፈቃድ ክፍያ ይከፈላል::

***የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ማለት:-*** ትርፍን መሰረት ያደረገ፣ ህዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅና ለማዝናናት ህጋዊ ሰውነት ባለው አካል የተቋቋመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው::

### *የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?*

- ✓ በአግባቡ የተሞላ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ፣
- ✓ የፕሮጀክት ጥናት፣
- ✓ የድርጅቱ አመራር አባሎች የስራ ልምድና የትምህርት ማስረጃ ሰነድ፣
- ✓ የድርጅቱ ተጠሪና የባለአክስዮች መታወቂያ ኮፒ/ቅጂ፣

ማንኛውም ድርጅት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ በ17 ቀናት ውስጥ አገልግሎት ማግኘት ይችላል::



### *የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት ምን ያህል ክፍያ ይጠይቃል?*

- ✓ የማመልከቻ ቅፅ ክፍያ ብር 50.00 /ሃምሳ ብር/፣
- ✓ የማመልከቻ ማጣሪያ ክፍያ ደግሞ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/፣
- ✓ ለኤፍ.ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ብር 75,000.00 /ሰባ አምስት ሺህ ብር/፣
- ✓ ለአጭር ወይም ለመካከለኛ ሞገድ ብር 50,000.00 / ሃምሳ ሺህ ብር/
- ✓ ለቴሌቪዥን ከሆነ ደግሞ ብር 150,000.00 /መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ይከፈላል::

***የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ማለት:-*** በአንድ በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም የጋራ ፍላጎት በሚያገናኛቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፍላጎት የተቋቋመና በማህበረሰቡ የሚተዳደር እና የሚመራ ለትርፍ ያልቆመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው::

### *የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?*

- ✓ በአግባቡ የተሞላ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣
- ✓ የአመልካቹ ድርጅት የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣
- ✓ የፕሮጀክት ጥናት፣
- ✓ ማህበረሰቡን የሚወክሉ የቦርድ አባላት አመራረጥን የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ፣
- ✓ የማህበረሰቡን አባላት ፊርማ የያዘ ሰነድ፣
- ✓ ማህበረሰቡን የሚገኝበት የአስተዳደር አካል የድጋፍ ደብዳቤ፣ ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የተፃፈ ፕሮሚሰሪ ደብዳቤ፣ በዚህ መሰረት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በ19 ቀናት ውስጥ የማህበ ረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ይሰጣል ::